# አታስብ ይሉኛል !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)








ማሰብ ማሰላሰል - ማጤን ማውጣት ማውረድ፤
ባ'ይምሮ መፀነስ - ሃሳብን ማዋለድ፤
ከምናብ ጓዳ ውስጥ - ምስጢርን ፈልፍሎ፤
ያይምሮ መረዋን - ማንኳኳት ደውሎ ፡፡
መላ ማፈላለግ - እንዲህ ቢሆን? ማለት ፤
አይምሮን ኮትኩቶ - ዕውቀት ዘርቶ ማምረት፤
ባ'ንዱ ውስጥ ሌላው_ በሌላው ውስጥ አንዱ_ እንዳለ መረዳት፡፡

ግና !

በማሰቢያቸው ላይ - ቁጭ ብለው የዋሉ፤
ለምን ?! እንዴት?! - ብለው መጠየቅ ያልቻሉ፤
በነሱ መክሊት ልክ - ማሰቤን ገድበው፤
አታስብ ይሉኛል - ማሰብ ወንጀል አርገው፡፡

መፈለግ ፤

ተጨንቆ ተጠቦ - ለሊት እንቅልፍ አ'ቶ፤
ልዩ ሃሳብ ማፍለቅ - አይምሮን ኮትኩቶ፤
ምሥጢሩን መርምሮ - ሥሪቱን መረዳት፤
ዕውቀት አጎልብቶ - ልዩ ጥበብ ማግኘት፤
ባ'ይምሮ ጓዳ ውስጥ - ገብቶ ማንጎዳጎድ፤
መቃኘት መማተር፤ - ማለት ነው ጉድ ጉድ ፡፡

ታዲያ !

የማሰብ ምሥጢሩ_ ውሉ ያልገባቸው፤
ያይምሯቸውን በር - ጥርቅም አርገው ዘግተው፤
ማሰላሰል ትተው - ቁጭ ብለው የዋሉ፤
ገና ከመባቻው - ማሰብ ያልታደሉ፤
ሃሳቤን ገድበው - አንደበቴን ዘግተው፤
አታስብ ይሉኛል ማሰብ ወንጀል አርገው፡፡

ማስተዋል፤

የመሬትን ሥሪት - የጨረቃን ውበት፤
ርቀት የከዋክብት - የፀሐይን ሙቀት፤
የተራራን ኩራት - የውቅያኖስን ጥልቀት ፤
የጉም ጥጥ ፈተላ - የበረዶን ንጣት፤
የሳተ ጎሞራ - የሙብረቅን ቁጣ፤
የበሽታ ዘሩ - ከየት እንደመጣ፤
ያየሩን ሹክሹክታ - የ'ግዜርን ዝምታ፤
የወፎች ዝማሬ - የዛፎች እስክስታ፤
ከየት መጣ?! ብሎ ጥያቄ መጠየቅ፤
ከኔም፤ ካንተም፤ ከሱ - አዲስ ሃሳብ ማፍለቅ፤
የነጠረ ሃሳብ ካይምሮ እንዲጨመቅ ።

ዛዲያ !

የ'ግዜር ምስልነቱ - ፍጥረቱ ያልገባቸው፤
ሕሊናውን ነፍጎ - ሆዱን ያደላቸው፤
መኖር ማለት ማሰብ - መሆኑን ዘንግተው፤
ሃሳብ ከወቂቱ - ሙጥጥ ያለባቸው፤
አታስብ ይሉኛል ሃሳብ ነጥፎባቸው።

መመርመር ፤

መቃኘት መማተር ! - ገብቶ ማገላበጥ ፤
ከፍቶ ማንጎዳጎድ - ባይምሮ ጓዳ ውስጥ፤
አቧራን አራግፎ - ድሩን መበጣጠስ!
ጥርት ያለ ሃሳብ - እስቲፈልቅ ድረስ።
ዝገቱን ማስወገድ - ጥቀርሻውን ማጽዳት፤
አይምሮን መርምሮ - ሥሪቱን መረዳት፤
በሳሉን ጠብቆ - ባለው ላይ መገንባት፤
ከ'ኔም ካንተም - ከ'ሱ ባንድላይ ሠንቆ፤
የነጠረ ሃሳብ - ሌላ ማፍለቅ ጨምቆ።

እናማ !

አምላክ የቸረኝን - ከጥዋቱ ስፈጠር፤
ከማሰቡ በዛ - ከዕንቅልፉ ቆንጠር፤
ከዕሽታው ቀንሶ - ከጥያቄው ጨመር፤
መማር መመራመር - ማሰቤን ገድበው፤
ይሉኝ ጀምረዋል ማስተዋል ወንጀል ነው ።

መደመም፤

መደነቅ፤ መገረም! - ማጤን ማሰላሰል፤
ባይምሮ ጓዳ ውስጥ - ሃሳብን ማብሰልሰል፤
እንዲህ ቢሆን ብሎ - ብልጭታ መፈንጠቅ፤
ተግቶ መላ መምታት - አዲስ ሃሳብ ማፍለቅ፤
ፍቅር ወንድማማች - አንድነት እንዲበቅል፤
አእምሮን ኮትኩቶ - ዕውቀትን ነው መትከል፤
መታነጽ በትምʼርት - ልዩ ጥበብ ማግኘት፤
ባʼንዱ ውስጥ ሁሉም_ በሁሉም ውስጥ አንዱ_ እንዳለ መረዳት።

ግና !

መሆኑ ያልገባቸው - መኖር ማለት ማሰብ ፤
ያልተጻፈ መጻፍ - የተጻፈ ማንበብ፤
ማዳመጥ መናገር - ማስረዳት መጠየቅ ፤
ሃሳብን በሃሳብ - መሳል ማሞሻለቅ፤
መናገር መተቸት - ማሰቤን ገድበው ፤
አታስብ ይሉኛል - ማሰብ ወንጀል አርገው።

ጥቅምት 27 ቀን 2009 ዓ.ም. (Nov. 7/2017)

ለእስክንድር ነጋ፤ ለአንዱዓለም አራጌ፤ ለተመስገን ለደሳለኝ፤ ለአንዳርጋቸው ጽጌ፤ለውብሸት ታዬ፤ ለዶ/ር መረራ ጉዲና፤ ለበቀለ ገርባ፤ ለዞን ዘጠኝ ጦማርያን፤ እንዲሁም ሌሎች ለሃሳብ ነፃነት፤ ለሰብአዊ መብት መከበርና፤ ለእኩልነት ብዕራቸውን ለሚያነሱ፤ ወንድሞቼና እህቶቼ ማስታወሻ ትሁንልኝ ።



